# ★ ዴሞክራሲያ ★

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ዴሞክራሲያዊ) ልሣን*

ቅጽ 41 ቁ.1 ሐምሌ 2006


## በጽናት መቆም ለዓላማ ስኬት መሠረት ነው!

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ከተመሠረተ 42 ዓመት፣ ራሱን ይፋ ካወጣ ደግሞ 39 ዓመት ሆኖታል። ኢሕአፓ ከምሥረታው ጀምሮ ይዟቸው የተነሳቸው ሕዝባዊ ጥያቄዎች ዛሬም አንገብጋቢነታቸው የሚያጠያይቁ አይደለም። ዋና ዋናዎቹ በሕዝብ ሙሉ ፈቃድ የተመረጠ ዴሞክራሲያዊ መንግሥት መመሥረት፣ የሕዝብ ያለገደብ የመደራጀትና በሕጋዊ መንገድ የዜግነት ግዴታቸውን ማከናወን፣ የብሄረሰቦች ሙሉ ዴሞክራሲያዊና ባህላዊ መብቶች መከበር፣ የሃይማኖቶች እኩልነትና የመንግሥት ከጣልቃገብነት መታቀብ፣ የኑሮ ውድነትን የሚቆጣጠርና ፍትሃዊ የኤኮኖሚ ፖሊሲ መተግበር፣ የሴቶች መብት መከበር የሚሉት በዋናነት ሊጠቀሱ ይችላሉ።

በነዚህ አራት አሥርተ-ዓመታት፣ ሀገራችን በሁለት መንግሥታት አገዛዝ ሥር ብታልፍም፣ ጥያቄዎቹ እስካሁን ድረስ መልስ አላገኙም። እንዲያውም ፓርቲው ሲመሠረት ያልነበሩ ችግሮች፣ ወይም በመጠናቸውና በዓይነታቸው ቀላል የነበሩ የያኔ ችግሮች በአሁኑ አገዛዝ ዘመን ተባብሰው እንደሚገኙ ፀሐይ የሞቀው ሃቅ ነው። ለምሳሌ በብሄረሰቦች መካከል የነበረውን ወዳጅነትና የኢትዮጵያዊነት ትስስር በሚያፈርስና በሚያደፈርስ መልኩ አገዛዙ ያካሄዳቸው ትንኮሳዎችና ማፈናቀሎች መጥቀስ ይቻላል። ፓርቲው ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ በጽናት የታገለላቸውን ሕዝባዊ ጥያቄዎች ስንመረምርና ምላሽ አለማግኘታቸውን ስንመለከት ሁለት እርምጃ ወደኋላ መሄዳችንን የሚከተሉት ነጥቦች ፍንትው አድርገው ያሳያሉ።

1. በሕዝብ ፈቃድና ይሁንታ የሚመሠረት መንግሥት ጥያቄ፤

የደርግን አምባገነን አገዛዝ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች፤ የሲቪል መንግሥት በሕዝብ ምርጫ እንዲመሠረት ቢጠይቁትም፤ አሻፈረኝ አለ። ሌላው ቀርቶ ደርግ ራሱ ለጠቅላይ ሚኒስቴርነት ያጫቸው አቶ ሃዲስ ዓለማየሁና ልጅ ሚካኤል እምሩ የሰጡትን የሕዝባዊ መንግሥት መመሥረት ምክርና ከደርጉም ውስጥ የሀገሪቱ ርዕሰ-ብሄር የነበሩት ጀኔራል ተፈሪ በንቲ ያቀረቡትን የመቻቻል ፖለቲካ ተግባራዊ ለማድረግ ፈቃደኛ ባለመሆኑ በሀገሪቱ የደረሰውን እጅግ አሳዛኝ ተግባር በመራራ ታሪክነቱ ሲታወስ የሚኖር ነው። በደርግ ምትክ የተተከለው የህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ በግብር ከደርግ ጋር ተመሳሳይ ሲሆን የውጭ መንግሥታትን ዳረጎት ለማግኘት ሲል በየጊዜው በሚያደርጋቸው የይስሙላ ምርጫዎች ባለፉት 23 ዓመታት ራሱን መልሶ መላልሶ ሥልጣን ላይ አስቀምጧል።

2. የሕዝብ በነፃነት የመደራጀት መብት አለመከበር፤

ደርግ ኢሕአፓን በሕገወጥነት ፈርጆ ማሳደዱ፤ ሕዝብም ደጋፊው ካልሆነ በስተቀር ሰላማዊ የዜግነት ኑሮ መኖር እንዳልቻለና ሀገራችንንም ለመውጣት አዳጋች ከሆነባት አዘቅት ውስጥ አስገብቶ እንዳለፈ የምናስታውሰው ነው። በህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝም፤ ነፃ የሠራተኛ ማኅበር፤ ነፃ የመምህራን ማኅበር፤ በራሱ የተደራጀ የተማሪ ማኅበር...ወዘተ መመኘት ከእባብ እንቁላል እርግብ እንደመጠበቅ ሆኗል። ባንፃሩ፤ ለተመልካች ነፃ የሚመስሉ፤ ነገር ግን ህወሓት/ኢህአዴግ እንደ ጭቃ ጠፍጥፎ የሠራቸው "ታማኝ" ድርጅቶችን መቀፍቀፉ ይታወቃል። ፓርላማ ተብዬውም ቢሆን ከአንድ የተቃዋሚ አባል በስተቀር ሌሎቹ ሁሉ የአገዛዙ ፓርቲ አባሎች በመሆናቸው በይዘትም በመልክም ከደርግ ጋር ለተመሳሳይነታቸው ጉልህ ማስረጃ ነው።

3. የብሄረሰቦች መብት መከበር፤

ኢሕአፓ በመርሃ-ግብሩና በአራት አሥርተ-ዓመታት ትግሉም የብሄረሰቦች መብት እንዲከበር ያላሰለሰ ትግል አድርጓል፤ መስዋእትነትም ከፍሏል። ደርግ በጦርነት ብቻ ለመፍታት የጦርነት ነጋሪቱን ሲጎስም ኢሕአፓ በሰላማዊና በዴሞክራሲያዊ መንገድ ይፈታ ብሎ ታግሏል። በማርክሳዊ ርዕዮተዓለም በሚመራበት ጊዜም የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች ሙሉ መብት ቢታወቅ፡ “እንገንጠል” የሚሉ እንኳን ቢኖሩ መብታቸውና እኩልነታቸው በተራማጅ ሥርዓት ከተረጋገጠ፤ ጽንፈኛ ጥያቄያቸው አድሃሪ እንደሚሆን

አሳይቷል። ከዚያም መርሃ-ግብሩን አሻሽሎ፤ ኢ.ሕአፓ ብሄረሰቦች በአንዲት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ውስጥ የውስጥ አስተዳደራቸውና ባህላዊ እሴቶቻቸውን የማስከበር መብታቸው በታወቀባት አገር መኖር እንደሚችሉ አስተምሯል። ይህ ሃቅ ባለፉት ሁለት አሥርተ-ዓመታት ህወሓት/ኢህአዴግ እየመረረውም ቢሆን እንዲቀበለው ስለተገደደ "ከጳጳሱ በላይ ሃይማኖተኛ" እንዲሉ "የባንዲራ ቀን" እያለ በየዓመቱ ለማጭበርበር ሞክሯል። በተግባር ግን አንቀጽ 39ን የመሰለ ፀረ-ኢትዮጵያ አንቀጽ በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ ከማስፈሩም በላይ የአኙዋክና የአማራ ብሄረሰቦች አባላትን ለረጅም ዓመታት ከኖሩበት ቀየ እያፈናቀለ፤ የኦሮሞና የሶማሌ ብሄረሰብ ተወላጅ የሆኑትን በእስር ቤቶቹ እያጎረ ለብሄረሰብ መብት የቆምኩ ነኝ እያለ ያላግጣል።

4. የሃይማኖቶች እኩልነትና መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አለመግባት፤

ኢ.ሕአፓ በሃይማኖት እኩልነት እንዲሁም መንግሥትና ሃይማኖትን የመለያየት ጽንሰ-ሃሳብ ገና ከጠዋቱ ጀምሮ ከታገለላቸው ዓላማዎች አንዱ ነው። በእስልምና ሃይማኖት ላይ ይደረግ የነበረውን አድሎ በመረዳት መንፈሳዊ በዓሎቹ እንደ ክርስቲያን ዕምነት ተከታዮች በዓሎች ሁሉ ብሔራዊ በዓሎች እንዲሆኑ ከሙስሊምና ከተራማጅ ክርስቲያን ወገኖቹ ጋር ታግሎ፤ ለተግባራዊነቱም አስተዋፅዖ አድርጓል። ህወሓት በዚህ ጥያቄ ላይ "ከእኔ በላይ ዴሞክራት ለአሳር" እያለ ሲፎክር ከሰነባበተ በኋላ ፈታኙ ወቅት የመጣበት ባለፉት ጥቂት ዓመታት ነው ማለት ይቻላል። በሃይማኖት ጉዳዮች ላይ እራሱ ባፀደቀው ሕገ-መንግሥት ውስጥ ያሰፈረውን በመጣስ የሙስሊሙን ኅብረተሰብ "የሚበጃችሁን እኔ አውቅላችኋለሁ" በማለት በሃይማኖት የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ገብቷል። የሙስሊሙም ኅብረተሰብ "የለም፤ አታውቅልንም፤ እኛው በራሳችን መንገድ ሃይማኖታችንን እንመራለን፤ የሚመሩንም ሰዎች በነፃነት እንመርጣለን" በማለት፤ እነሆ ትውልድን በሚያኮራ መልኩ ያልተቋረጠና ተከታታይ ሰላማዊና መንፈሳዊ ትግል አድርገዋል፤ አሁንም በማድረግ ላይ ይገኛሉ። ይህ ትግል ከአጠቃላይ የዴሞክራሲና በሰላማዊ መንገድ ሕዝብን የሥልጣን ባለቤት ለማድረግ ከሚደረገው ትግል ጋር መቆራኘቱን ሁኔታው የግድ ይላል። በዚህ በኩል ሁሉም አገር ወዳድ ኃይሎች አገዛዙ በሚያናፍሰው የሃሰት "የአሸባሪነት" ክስ ፕሮፓጋንዳ ሳይዘናጉ የኢትዮጵያን ሕዝብ ትግል በአንድ አቅጣጫ ማስኬድ የወቅቱ ግዴታቸው እንደሆነ ሊገነዘቡ ይገባል።

5. ፍትሃዊ የኤኮኖሚ ፖሊሲና የኑሮ ውድነት ጉዳይ፤

ኢሕአፓ በትግል ታሪኩ ከደሃው ወገኑ ጎን የቆመና ድህነትና ረሃብ ከሀገራችን እንዲወገዱ በግምባር ቀደምነት የታገለና ዛሬም የሚታገል ፓርቲ ነው። ደርግ የኅብረተሰቡን ክፍሎች ሁሉ በሱ አምሳል ለመቅረጽ በማደራጀቱ የመሬት አዋጅና ሌሎችም ፖሊሲዎች ለሕዝቡ ሊያስገኙ የሚችሉትን ጥቅሞች እንዳያገኙ አድርጓል። አገሪቷም በጦርነት በመታመሷ ድህነትና ረሃብ መታወቂያዋ ሆነው ኖረዋል። የህወሓት/ኢህአዴግ "ልማታዊ መንግሥት" ነኝ እያለ ራሱን ቢያሞካሽም፤ ዛሬ በሀገራችን ድህነት ከመቼውም በከፋ ሁኔታ ላይ እንደሚገኝና የኑሮ ውድነትን ማውራት ለቀባሪው ማርዳት ይሆናል። ህወሓት/ኢህአዴግ ለውጭ ባለሃብቶች በርካሽ የሚቸረችረውን የሀገሪቱን ለም የእርሻና የደን መሬት ጉዳይ መልሶ ሊመረምረው ይገባል እንላለን። ዛሬ በሀገሪቱ ውስጥ ተንሰራፍቶ የሚገኘው ሙስና ገዥው ፓርቲ ከላይ እስከታች የተዘፈቀበት ነው። ጥቂት ምርጦች የሀገሪቱን ሃብት "ኤፈርት" በሚል ሰበብ በሀገር ውስጥና በውጭ አገር ባንኮች አከማችተው ዓይን ያወጣ ዘረፋ የሚያካሂዱበት ጊዜ ላይ ደርሰናል።

6. የሴቶች መብት መከበር፤

በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ ሴት እህቶቻችንና እናቶቻችንን ወደትግሉ በማምጣት ኢሕአፓ የጎላ ሚና ተጫውቷል። በገጠር ለአቅመ-ሄዋን ያልደረሱ የልጃገረዶች ባህላዊ ጋብቻ እንዲቀር የቻለውን ሁሉ አድርጓል። የሴቶች ደመወዝ ክፍያ ከወንዶች እኩል እንዲሆን ታግሏል፤ ሴቶች በፓርቲው ውስጥ የጎላ ሚና እንዲጫወቱ ሁኔታዎችን አመቻችቶ አታግሏል፤ ከጎናቸው ቁሞ ታግሏል፤ አሁንም ለዚህ ክቡር ዓላማ ትግሉን ይቀጥላል። ዛሬ የሴቶች መብት በሚያሳዝን ደረጃ ላይ ይገኛል። ገላቸውን እንዲሸጡ የሚገደዱበት ኢ-ሰብአዊ ሁኔታ ዛሬም በከፋና በአስቃቂ መልኩ ተስፋፍቷል። እናቶች በኑሮ ውድነት ምክንያት ልጆቻቸውን ማሳደግ ስላልቻሉ በማደጎነት ለውጭ ዜጎች መስጠት የተለመደ ሆኗል። ሕፃናቱ በአንዳንድ የውጭ ዜጎች እንደሚበደሉና እስከመገደልም እንደደረሱ በሃዘን እየሰማን ነው። ወጣት ሴቶች ለሥራ ወደ መካከለኛው ምሥራቅ እየሄዱ እጅግ እየተሰቃዩና በሚያሳዝን ውርደት ላይ እንደሚገኙ እያየንና ብዙዎች ከአገር ተሰደው ሲወጡ በባህርና በመንገድ ብዙ አደጋዎች እንደሚገጥሟቸውም አይተናል።

7. በኅብረት ግምባር ስለመታገል አስፈላጊነት

ደርግ ከጥቂት አሥርተ-ዓመታት በፊት ላቀረበለት የይስሙላ በግምባር የመሳተፍ ጥያቄ ኢ.ሕ.አ.ፓ የሰጠው ምላሽ፤ ኢ.ሕ.አ.ፓ ብቻ ሳይሆን ሌሎችም የብሄረሰብ ድርጅቶችና አገር አቀፍ ድርጅቶች የሚሳተፉበት ዴሞክራሲያዊ ግምባር እንዲመሠረት ነበር። ደርግ ግን የኢ.ሕ.አ.ፓን ምላሽ ውድቅ አድርጎ፤ ጦርም ከመዘዘበት በኋላ በ1993 ዓ.ም የመጀመሪያውን ሰፊና የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶችን ያካተተውን የኅብረት ግምባር ማለትም የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ቅንጅትን (ኢ.ዴ.ኃ.ቅን) ከመሠረቱት ግንባር ቀደም ድርጅቶች አንዱ ሆነ። ከዚያ በኋላም በተመሠረቱት የኅብረት ግምባሮች - የዛሬውን ሸንጎ ጨምሮ - ኢ.ሕ.አ.ፓ በጋራ የመታገልን አስፈላጊነት በንድፈ ሃሳብ ብቻ ሳይሆን በገቢርም በንቁ ተሳታፊነት አርአያነቱን ያሳየና አሁንም እያሳየ የሚገኝ ፓርቲ ነው። ሀገራችን አሁን የምትገኝበት ሁኔታ እጅግ አሳሳቢ በመሆኑ አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያንና የተቃዋሚ ድርጅቶች ልዩነታቸውን አቻችለው በኅብረት ሀገራችንንና ሕዝባችንን እንድንታደግ ኢ.ሕ.አ.ፓ ዴሞክራሲያዊ ሀገራዊ ጥሪውን ያቀርባል።

አሻፈረኝ ብሎ በአንድነትና በጽናት የተነሳ ሕዝብ ያቸንፋል!